## ምዕራፍ ፡ ፴፬ ።

ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ መረብን ፡ አልፈው ፡ አሥመራን ፡ ያሊያዙበት ፡ ምክንያት ፡ የሮማው ፡ ጳጳስ ፡ ስለ ፡ ኢጣሊያ ፡ ምርኮኞች ፡ የጻፉት ፡ ደብዳቤ ፡ — ስለ ፡ ዕርቅና ፡ ስለ ፡ ወሰን ፡ ክለላ ፡ የተደረገ ፡ ውል ። ስለ ፡ ምርኮኞቹ ፡ መለቀቅ ።

ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በፊት ፡ ወዳጅ ፡ መስሎ ፡ በኋላ ፡ ጠላት ፡ ሆኖ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የነፃነት ፡ ልብስ ፡ ለመግፈፍ ፡ የመጣባቸውን ፡ ጠላታቸውን ፡ መገሠመሪያ ፡ አምባላጌ ፡ ቀጥሎ ፡ መቀሌ ፡ ላይ ፡ በመጨረሻም ፡ ስሙ ፡ ጠላትን ፡ እሚያሳፍረው ፡ ኢትዮጵያን ፡ እሚያኰራው ፡ ዐድዋ ፡ ላይ ፡ በታላቅ ፡ ጦርነት ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ መረብን ፡ አሻግረው ፡ ተመለሱ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይህንኑ ፡ ጠላታቸውን ፡ ከአሥመራ ፡ አስወጥቶ ፡ ባሕርን ፡ አሻግሮ ፡ ማባረር ፡ ባሳባቸው ፡ ውስጥ ፡ ሳይመጣባቸው ፡ አልቀረም ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ አቅንተው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የጠቀለሉትና ፡ ጥንትም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ይገዛ ፡ የነበረው ፡ የያገሩ ፡ ነገድ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አንድነት ፡ ለመለየት ፡ የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ከውጭ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ በጦርነት ፡ መዳከም ፡ ይረባው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ የአውሳ ፡ ባላባት ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ታዛዥ ፡ ሆኖ ፡ እየገበረ ፡ የኖረውን ፡ የዐድዋ ፡ ጦርነት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ በኢጣሊያ ፡ ስብከት ፡ ተታሎ ፡ ሸፈተ ። እርሱንም ፡ ለመውጋት ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስና ፡ ደጃች ፡ ተሰማ ፡ ናደው ፡ ባዛዥ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ አበጋዝነት ፡ ሄደው ፡ ነበር ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ዐድዋ ፡ ላይ ፡ ድል ፡ ቢሆን ፡ እስከ ፡ ምጥዋ ፡ ድረስ ፡ አባረው ፡ ካሥመራ ፡ ሊያስወጡኝ ፡ የፈለጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ደግሞ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ሳልዋጋ ፡ አሥመራን ፡ አለቅም ፡ በማለት ፡ ለዚሁ ፡ በዐድዋ ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላይ ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ ከነበረው ፡ ከጄኔራል ፡ ባራቲዬሪ ፡ ይበልጥ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የሆነውን ፡ ጄኔራል ፡ ባልዲሰራን ፡ ካ፲፰ ፡ ሺሕ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ላከው ፡ ርግጥ ፡ ነበር ።

እውነት ፡ ነው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መረብን ፡ አልፈው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከጄኔራል ፡ ባልዲሰራ ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ ከአሥመራና ፡ ከምጥዋ ፡ በጭራሽ ፡ አጥፍተውት ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ባ፲፱፻



፳፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በጦርነት ፡ ለማጥቃትና ፡ የዐድዋ ፡ ብድሬን ፡ መለስሁ ፡ ብሎ ፡ ለመፎከር ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ከምቹ ፡ ሥፍራ ፡ ጋራ ፡ ባላጋጠመው ፡ ነበር ። ከከባድ ፡ ቀንበር ፡ በታች ፡ የተገዙትም ፡ ኤርትራውያን ፡ ለባዕድ ፡ ተላለፍን ፡ በማለት ፡ እየተበሳጩ ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ ጋራ ፡ ደም ፡ ባልተፋሰሱም ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ከዐድዋ ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ አሥመራ ፡ ውስጥ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ከመጣው ፡ አዲስ ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ቢዋጉ ፡ ድል ፡ ያደርጉ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አሁንስ ፡ ያን ፡ ጊዜስ ፡ በርግጥ ፡ የሚያውቀው ፡ ማን ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ምክንያትና ፡ ደግሞ ፡ የዛሬ ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊ ፡ ሊያውቀው ፡ የማይችለውን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ባሳባቸው ፡ ውስጥ ፡ የነበረባቸውን ፡ ችግር ፡ አመዛዝነው ፡ ይኸንኑ ፡ ድል ፡ ለሰጣቸው ፡ አምላክ ፡ ምስጋና ፡ አቅርበው ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ እንዳማረባቸው ፡ ምርኮኛቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ተመለሱ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የሮማው ፡ ጳጳስ ፡ ፲፫ኛ ፡ ልዮን ፡ በኢጣሊያ ፡ አገር ፡ ያሉት ፡ የምርኮኞቹ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ እያለቀሱ ፡ ስላስቸገሯቸውና ፡ ለራሳቸውም ፡ ወገኖቻቸው ፡ በመሆናቸው ፡ ምርኮኞቹ ፡ በነፃ ፡ እንዲለቀቁ ፡ ሲሉ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትነና ፡ ክርስቲያንነትን ፡ የተደገፈ ፡ የልመና ፡ ደብዳቤ ፡ አሲዘው ፡ ሞንሲኞር ፡ ማካሪዮንን ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ላኩ ። ከደብዳቤውም ፡ ይበልጡ ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ነው ።

«ለኀያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡
ሰላም ፡ ለርስዎ ፡ ይሁን ።

ክርስቲያናዊ ፡ በሆነው ፡ ልብዎ ፡ የምመክርዎትን ፡ አመዛዝነው ፡ የልግስና ፡ ሥራ ፡ እንዲያደርጉ ፡ እለምንዎታለሁ ።

የዚህ ፡ የዘመቻ ፡ ድል ፡ በእጅዎ ፡ ብዙ ፡ የኢጣሊያ ፡ ምርኮኞች ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶዎታል ፡ የነዚህም ፡ የኢጣሊያኖች ፡ መማረክ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ያሉትን ፡ በሺህ ፡ የሚቈጠሩትን ፡ የእናቶቻቸውንና ፡ የሚስቶቻቸውን ፡ የልብ ፡ ኀዘንና ፡ ጭንቀት ፡ ከማበርከት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ የግርማዊነትዎን ፡ ኀይልና ፡ ዝና ፡ ሊያስፋፉ ፡ አይችልም ። እኛም ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተቀበልነው ፡ አደራ ፡ እንደ ፡ ልጆቻችን ፡ ያኽል ፡ እንወዳቸዋለንና ፡ እነዚህን ፡ ምርኮኞች ፡ በቶሎ ፡ በነፃ ፡ እንዲለቋቸው ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴና ፡ በድንግል ፡ ማርያም ፡ ወይም ፡ በዓለም ፡ ካለው ፡ በሚወዱት ፡ ስም ፡ እለምንዎታለሁ ።

ኀያሉ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሆይ ፡

ይኸንንም ፡ የምለምንዎትን ፡ እንደ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ እንቢ ፡ ማለትዎ ፡ በመንግሥታት ፡ ፊት ፡ የተገለጸ ፡ አይሁን ፡ ይህችንም ፡ የተከበረች ፡ ደብዳቤዬን ፡ ለምስክር ፡ እታሪክዎ ፡ መዝገብ ፡ ያግቧት ።

በዚህም ፡ በሚያደርጉት ፡ የቸርነት ፡ ሥራ ፡ ርኅሩኅና ፡ የሁሉ ፡ አባት ፡ የሆነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክስዎታል ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ በብዙ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ሊያመሰግኑዎ ፡ ድምፃቸውን ፡ ያነሣሉ ፡ ከነዚሁም ፡ መዠመሪያዎቹ ፡ እኛ ፡ ነን ።

ይህ ፡ የልመና ፡ ቃል ፡ እንዲፈጸም ፡ በተስፋ ፡ ከመጠባበቅ ፡ ጋራ ፡ ልዑል እግዚአብሔርን ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ በቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ ላይ ፡ በረከቱን ፡ እንዲያወርድ ፡ እንጸልያለን ፡ ሮማ ፡ እቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጠገብ ፡ (እንደ ፡ ኤ. ቍ) ፡ ግንቦት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፺፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።

ፊርማ ፡ ልዮን ፡ ፒፒ ፡ ፲፫ኛ » ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ንግግር ፡ ልባቸው ፡ ቢነካ ፡ ከጦርነቱ ፡ ወዲህ ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ወሰኑና ፡ ስለ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ የታወቀ ፡ ውል ፡ አልተዋዋሉም ፡ ነበርና ፡ ውል ፡ ከማድረግ ፡ አስቀድሞ ፡ በዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ በእጃቸው ፡ ያለውን ፡ ምርኮኛ ፡ ለመልቀቅ ፡ የማይቻልበትን ፡ ምክንያት ፡ ገልጸው ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጥና ፡ የሚያጽናና ፡ ደብዳቤ ፡ አሲዘው ፡ ሞን ፡ ሲኞር ፡ ማካሪዮንን ፡ መልሰው ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ላኳቸው ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ዶክቶር ፡ ኔራሲኒ ፡ የሚባለው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሂዶ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋራ ፡ የዕርቅ ፡ ውል ፡ እንዲያደርግ ፡ ተልኮ ፡ መስከረም ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገባ ።

ቀጥሎም ፡ ስለ ፡ ዕርቁና ፡ ስለ ፡ ወሰኑ ፡ ባ፲፰፻፹፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ተዋዋለ ።

፩ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተደረገው ፡ ያለ ፡ ጦርነት ፡ ቀርቶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥትና ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ መካከል ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ የሚቈይ ፡ የወዳጅነትና ፡ የዕርቅ ፡ ውል ፡ ተደርጓል ።

፪ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ውጫሌ ፡ ላይ ፡ ተደርጎ ፡ የነበረው ፡ ውል ፡ በፍጹም ፡ ቀርቷል ።

፫ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ ያውቃል ።



፬ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስለ ፡ ወሰኑ ፡ በንግግር ፡ ቢስማሙ ፡ አሁንም ፡ ይህ ፡ ውል ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ የሚካለሉላቸውን ፡ ወኪሎቻቸውን ፡ አድርገው ፡ በስምምነት ፡ ይካለላሉ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ የመረብና ፡ የበለሳ ፡ ወሰን ፡ ይሁን ፡ ተብሎ ፡ ለጊዜው ፡ የተወሰነው ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ከበረ ፡ ይቈያል ፡ እንጂ ፡ አይሻርም ።

፭ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ወሰኑን ፡ በደንብ ፡ ሳይካለል ፡ በኤርትራ ፡ የያዘውን ፡ አገር ፡ ወይም ፡ ከያዘው ፡ አገር ፡ ቈርጦ ፡ ለመስጠት ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ይለቃል ፡ እንጂ ፡ ለሌላ፡ መንግሥት ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።

ይህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ውል ፡ ተዋውለው ፡ የውሉ ፡ ቃል ፡ ለኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ ተልኮለት ፡ ከተስማሙበት ፡ በኋላ ፡ ከምርኮኞቹ ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የመስኮብ ፡ ንጉሥ ፡ ኒኮላ ፡ ዛር ፡ የተወለዱበት ፡ ቀን ፡ ሲከበር ፡ ስለ ፡ እርሳቸው ፡ ክብር ፡ ፶ ፡ የኢጣሊያ ፡ እሥረኞች ፡ ተለቀው ፡ ነበር ፡ እንዲሁም ፡ የተረፉትን ፡ ምርኮኞች ፡ በነፃ ፡ ለቀዋቸው ፡ ካ፲፰፻፹፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፺ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጥር ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ሁሉም ፡ በዘይላ ፡ በኩል ፡ ተሳፍረው ፡ ወዳገራቸው ፡ ገቡ ። ከምርኮኞቹም ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ባዛኘ ፡ ዛማኔል ፡ ቤት ፡ በምሪት ፡ ይኖር ፡ የነበረው ፡ አልቤርቶኔ ፡ የሚባለው ፡ ጀኔራል ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ አብሮ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ምርኮኞቹ ፡ ከመነሣታቸው ፡ በፊት ፡ የዐድዋ ፡ ጦርነት ፡ ዕለት ፡ ከሞተው ፡ ከጀኔራል ፡ አሪሞንዲ ፡ የተማረከውን ፡ ሻምላውን ፡ ለቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ አስረክብለት ፡ ብለው ፡ ለጀኔራል ፡ አልቤርቶኒ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በፊታቸው ፡ አሰጡትና ፡ ተረክቦ ፡ ይዞ ፡ ሂደ ፡ ይኸውም ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክን ፡ ልበ ፡ ሰፊነትና ፡ ቅንነታቸውን ፡ ያስረዳል ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከምጥዋ ፡ እየገሠገሠ ፡ እስከ ፡ አምባአላጌ ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንዲሁም ፡ ከኤርትራ ፡ በስተምዕራብ ፡ በኩል፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየገፋ ፡ ሂዶ ፡ ከሰላን ፡ ሁሉ ፡ ይዞ ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በጦርነት ፡ ከመረብ ፡ ወዲያ ፡ እንዳሻገሩት ፡ እንዲሁም ፡ ደርቡሾች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በአጎርዳት ፡ እየወጉ ፡ ስላስቸገሩትና ፡ ኀይሉ ፡ ስለ ፡ ተዳከመ ፡ ለራሱ ፡ እስከ ፡ ሰብደራት ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ አስቀርቶ ፡ የከሰላን ፡ ግዛት ፡ ታኅሣሥ ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፺ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ለቀቀለት ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፫ ።

### የዓድዋ ፡ ድልና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡

ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደገለጽነው ፡ የዓድዋ ፡ ድል ፡ በኢጣልያ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ሽብርና ፡ ድንጋጤ ፡ ፈጥሯል ። የእንግሊዝና ፡ የፈረንሳዊ ፡ ያንዳንድ ፡ ክፍል ፡ ወታደር ፡ በእስያና ፡ በአፍሪካ ፡ በቀላል ፡ ጦርነት ፡ ሰፋፊ ፡ ግዛት ፡ ለየመንግሥታቸው ሲያተርፉ ፡ ኢጣልያንን ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ የመሰለ ፡ የመሸነፍ ፡ አደጋ ፡ ስለደረሰባት ፡ ይኸው ፡ ሁኔታ ፡ በዘመኑ ፡ ባለው ፡ በየመንግሥቱ ፡ ጋዜጣ ፡ እየተጠቀሰ ፡ ስለተጻፈ ፡ በኢጣልያኖች ፡ ዘንድ ፡ ሐፍረትና ፡ ቁጭት ፡ አሳድሮ ፡ ነበር ። በኢጣልያ ፡ አገር ፡ የሶሲያልስቱ ፡ ወገን ፡ ቀድሞውንም ፡ ጦርነቱ ፡ ቢቀርብን ፡ ይሻላል ፡ ይል ፡ ነበርና ፡ አሁንም ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ድል ከደረሰብን ፡ የኤርትራ ፡ ግዛት ፡ ለምለምና ፡ ፍሬያማ ፡ ስላልሆነ ፡ ኢጣልያን ፡ ገንዘብ ፡ ከማስወጣት ፡ በቀር ፡ የሚረባን ፡ ነገር ፡ የለምና ፡ ይለቀቅ ፡ ብለው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የቀሩት ፡ አማካሪዎች ፡ ይኸን ፡ አሳብ ፡ ስላልተቀበሉት ፡ የኤርትራን ፡ ግዛት ፡ እንዲከላከል ፡ ጀኔራል ፡ ባልዲሠራ ፡ ተላከ ፡ እርሱም ፡ ኤርትራ ፡ ከመጣ ፡ ወዲህ ፡ አዲስ ፡ ይዞ ፡ ከመጣው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በቀር ፡ ከአድዋ ፡ ጦርነት ፡ የሸሸውን ፡ ጨምሮ ፡ ፴ሺ ፡ የሚሆን ፡ ጦር ፡ አደራጅቶ ፡ ነበር ፡ በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ምናልባት ፡ የሚቻል ፡ ቢሆን ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ አገር ፡ መያዝና ፡ ያለፈውን ፡ የጦርነት ፡ ድል ፡ ለመበቀል ፡ እንዲያጠና ፡ ታዞ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ የኢትዮጵያን ፡ የውስጥ ፡ አንድነት ፡ የጦሩንም ፡ ኃይል ፡ ገምቶ ፡ ፹ሺ ፡ ጦር ፡ ካልተላከልኝ ፡ አይቻልም ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ሰጠ ፡ ይባላል ።

ስለዚህ ፡ የኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ የዚህን ፡ እንደገና ፡ አገርን ፡ የመውረርና ፡ በጦርነት ፡ የመበቀልን ፡ ነገር ፡ ተወና ፡ ባለፈው ፡ ያየነውን ፡ ውል ፡ መላክተኛውን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ድረስ ፡ ልኮ ፡ ተዋዋለ ። በውሉም ፡ ውስጥ ፡ በውጫሌ ፡ ውል ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ የሚለውን ፡ ክርክር ፡ ሁሉ ፡ ሽሮ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ ማወቁን ፡ በግልጽ ፡ ፈረመ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የዚህኑ ፡ ውል ፡ ውሳኔ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ለወዳጆቻቸው ፡ ለፈረንሳዊና ፡ ለመስኮብ ፡



መንግሥት ፡ እንደዚሁም ፡ ለእንግሊዝና ፡ ለሌሎቹም ፡ አስታወቁ ። ስለዚህ ፡ መንግሥታቱ ፡ ከዚህ ፡ ውል ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስቴሮቻቸውን ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እየላኩ ፡ ያስቀምጡ ፡ ዠመር ።

ሀ — የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ሙሴ ፡ ሌዎንስ ፡ ላጋርድን ፡
ለ — መስኮብ ፡ ገኔራል ፡ ቭላሶውን ፡
ሐ — እንግሊዝ ፡ ሊዬተና ፡ ኮሎኔል ፡ ዠን ፡ ላን ፡ ሐሪንግተንን ፡
መ — ኢጣልያም ፡ ካፒቴን ፡ ፌዴሪኮ ፡ ቺኮዲኮላን ፡ ላኩ ።

እነዚህም ፡ ከየራሳቸው ፡ መንግሥት ፡ የተላኩበትን ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አቅርበው ፡ ሌጋሲዮናቸውን ፡ እየከፈቱ ፡ ተቀመጡ ።

በዓድዋ ፡ ጦርነት ፡ የኢጣልያ ፡ ጦር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጦር ፡ አሸንፎ ፡ ቢሆን ፡ አገሩን ፡ ሁሉ ፡ በየጊዜው ፡ ወሮ ፡ በመጨረስ ፡ ለዘለቄታ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ሊያደርገው ፡ ይችል ፡ ነበር ፡ ኢትዮጵያም ፡ በሚመጣው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለመነሻና ፡ ነፃነቷን ፡ ለማግኘት ፡ በቂ ፡ ምክንያትና ፡ ኃይል ፡ አታገኝም ፡ ነበር ። የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ ሲሸነፍም ፡ ፈረንሳዊ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ሲል ፡ ከኢጣልያ ፡ ይዋጋል ፡ ተብሎ ፡ አይጠረጠርም ። ከዓድዋ ፡ ድል ፡ በኋላ ፡ በ፲፰ኛው ፡ ዓመት ትልቁ ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በተነሣም ፡ ጊዜ ፡ ኢጣልያ ፡ በ፳ኛው ፡ ዓመት ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ጓደኛ ፡ ሆኖ ፡ ከእንግሊዝና ፡ ከፈረንሳዊ ፡ ጋር ፡ ጀርመኖችን ፡ ስለወጋና ፡ ከአሸናፊዎቹ ፡ ወገን ፡ ስለተቆጠረ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የመቀስቀሻው ፡ ጊዜ ፡ የተዘጋ ፡ ይሆን ፡ ነበር ፤ ስለዚህ ፡ በርትቶ ፡ የተዋጋውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ የድል ፡ አድራጊነቱን ፡ ዕድል ፡ የተካፈሉትን ፡ መሳፍንት ፡ ማመስገን ፡ ይገባል ። ምክንያቱም ፡ እነዚህ ፡ ወይም ፡ ከእነዚህ ፡ አንዱ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክን ፡ እንደሸዋ ፡ ንጉሥና ፡ እንደ ባዕድ ፡ ቆጥረው ፡ የራሳቸውን ፡ ምኞት ፡ በዚህ ፡ አስቸጋሪ ፡ ጊዜ ፡ ለመፈጸም ፡ በመሞከር ፡ ተለይተው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እነዚህም ፡ እንሸፍት ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክም ፡ ለምን ፡ በማለት ፡ የውስጥ ፡ ግጭት ፡ ተነሥቶ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ለኢጣልያ ፡ ጦር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይጠቅመው ፡ እንደነበረ ፡ ለመመልከት ፡ ግልጥ ፡ ነበር ። የኢጣልያም ፡ የጦርና ፡ የፖለቲካ ፡ መሪዎችም ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ እየተላላኩ ፡ ዠሮዋቸውን ፡ ከፍተው ፡ የጠበቁት ፡ ይኸንኑ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ አንድነት ፡ የመኳንንቱና ፡ የመሳፍንቱ ፡ ኅብረት ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ታማኝነት ፡ ከመቸውም ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ የጠበቀ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ኢጣል

ያኖች ፡ አቆብቁበው ፡ የጠበቁት ፡ ነገር ፡ ብቅ ፡ ሊልላቸው ፡ አልቻለም ። ጦርነ ቱም ፡ ቀላል ፡ አልነበረም ፡ የኢጣልያኖችም ፡ ብዛታቸውና ፡ የመሣሪያቸው ፡ ጥራት ፡ እነርሱም ፡ ድሉን ፡ ለማግኘት ፡ ያደረጉት ፡ ትጋትና ፡ ትግል ፡ ዋዛ ፡ አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገበየሁ ፡ ያሉ ፡ ዠግና ፡ የሹማም ንት ፡ ወታደሮች ፡ ያሉበት ፡ ጦር ፡ በዋዛ ፡ አይፈታምና ፡ የሞቱትም ፡ በሕይ ወት ፡ የተመለሱትም ፡ ምክርና ፡ መላ ፡ አዋቂዎቹም ፡ የጦር ፡ አርበኞቹም ፡ ተባብረው ፡ ያሳዩት ፡ የወታደርነትና ፡ የፖለቲካ ፡ አንድነት ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ሰብሮ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ የክብር ፡ አክሊል ፡ ደፋለት ።


## ምዕራፍ ፡ ፴፮ ።

## ሱማልያና ፡ ሱማሌዎች ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ ለዚህ ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ፡ ለተደረገው ፡ ጦርነት ፡ የረዳውን ፡ ኤርትራን ፡ ካገኘ ፡ ወዲህ ፡ እንዲሁም ፡ በኢ ትዮጵያ ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ አገር ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ በነገሩ ፡ እንዲያስብበት ፡ በአደንና ፡ በዛንዚባር ፡ በቆንሲልነት ፡ ያስቀመጣቸውን ፡ ካፒቴን ፡ አንቶኒዮ ፡ ቼኪንና ፡ ካባሊዬሪ ፡ ፌሎናርዲን ፡ አዟቸው ፡ ነበር ።

የበናዲርን ፡ ግዛት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ሲገዙት ፡ ከቈዩ ፡ ወዲህ ፡ የመስቃጥ ፡ ሡልጣን ፡ ይገዛው ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የመስቃጥ ፡ ሡልጣን ፡ ኀይሉ ፡ ስለ ፡ ደከመ ፡ ግዛቱ፡ ለዛንዚባር ፡ ሡልጣን ፡ ተላለፈ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ካፒቴን ፡ አንቶኒዮ ፡ ቼኪ ፡ በዚሁ ፡ በህንድ ፡ ውቅያ ኖስ ፡ ዳርቻ ፡ መሬት ፡ ቈርጦ ፡ እንዲሰጠው ፡ ሡልጣኑን ፡ ጠይቆት ፡ ከከለከ ለው ፡ በኋላ ፡ ባ፲፰፻፹፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የንግድ ፡ ውል ፡ ብቻ ፡ ተዋዋለ ። ስለዚህ ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ በመርከብ ፡ ንግድን ፡ ምክንያት ፡ አድርገው ፡ የሚመ ጡት ፡ ጣሊያኖች ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ከሚገኙት ፡ ሡልጣኖችና ፡ የሱማሊያ ፡ ሹማ ምቶች ፡ ጋራ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ማድረግ ፡ ዠመሩ ። ወዲያውም ፡ ከመ ቃዲሾ ፡ በስተምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ የሱፍ ፡ ዐሊ ፡ የሚባለው ፡ የኦቢያ ፡ ሡልጣን ፡ ከላይ ፡ ዐረቦች ፡ እየመጡ ፡ ያውኩት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ድጋፍ ፡ ለመፈ ለግ ፡ ሲል ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ የኢጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ጠባቂ ፡ ብቻ ፡ እን



የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ የጦር ፡ ኀይል ።

ዲሆነው ፡ ውል ፡ ተዋዋለ ። እሱም ፡ ይህን ፡ ከተዋዋለ ፡ ወዲህ ፡ የርሱ ፡ ባላንጣ ፡ ዑስማን ፡ መሐመድ ፡ የሚባለው ፡ የሚጁሪቲን ፡ ሡልጣን ፡ እንዲሁ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ጠባቂ ፡ እንዲሆን ፡ ባ፲፰፻፹፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ተዋዋለ ። የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ የሚገኘውን ፡ ሀብት ፡ እየወሰደ ፡ ለሡልጣኖች ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ ባመት ፡ ሺህ ፡ ፳፻ ፡ ብር ፡ ሊሰጥ ፡ ፈረመላቸው ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እነዚህን ፡ እላይ ፡ የተጻፉትን ፡ አገሮች ፡ በጠባቂነት ፡ ስም ፡ ካገኘ ፡ ወዲህ ፡ ከመቃዲሾ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የወረሼክን ፡ አገር ፡ ለመያዝ ፡ በመርከብ ፡ ወታደሮች ፡ አውርዶ ፥ ጥቂት ፡ ሳይቈይ ፡ ወዲያው ፡ የዚሁ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ ስለ ፡ ወጓቸው ፡ በመርከብ ፡ ተሳፍረው ፡ ወደ ፡ መጡበት ፡ ስፍራ ፡ ተመልሰው ፡ ሸሹ ። በኋላ ፡ ግን ፡ በካባሊዬሪ ፡ ሬሎናርዲ ፡ አዝማችነት ፡ ወታደርም ፡ መሣሪያም ፡ ጨምረው ፡ መጥተው ፡ ጦርና ፡ ቀስት ፡ ከያዙት ፡ ሱማሌዎች ፡ ጋራ ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ባለጠመንዣዎቹ ፡ ባለቀስቶቹን ፡ አሸንፈው ፡ ስላባረሯቸው ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከወዲህ ፡ ከኬንያ ፡ ድንበር ፡ ከጁባ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ በርበራ ፡ ግዛት ፡ ወሰን ፡ ድረስ ፡ በጠባቂነት ፡ ስም ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ለዳር ፡ ግዛቱን ፡ አራዝሞ ፡ ይኸንኑም ፡ ለየመንግሥታቱ ፡ አስታወቀ ።

የእንግሊዝና ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በያዙት ፡ አገር ፡ በወሰን ፡ ስለ ፡ ተገናኙ ፡ ስምምነት ፡ አድርገው ፡ ወሰኑን ፡ ከተካለሉ ፡ በኋላ ፡ በህንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ዳርቻ ፡ የሚገኙት ፡ የብራዋ ፡ የሜርካ ፡ የበናዲር ፡ የመቃዲሾ ፡ የወረሼክ ፡ የባሕር ፡ በሮች ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ይህን ፡ አገር ፡ በበላይነት ፡ ይገዛ ፡ ለነበረው ፡ ለዛንዚባሩ ፡ ሡልጣን ፡ ባ፲፰፻፹፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በነሐሴ ፡ እንደ ፡ ተዋዋሉት ፡ ባመት ፡ ፻፳ ፡ ሺህ ፡ ሩቢስ ፡ ሊከፍለው ፡ ውል ፡ ተደረገ ።

ካፒቴን ፡ ቼኪ ፡ አፍጎይ ፡ ሄዶ ፡ ከጋለዲ ፡ ሡልጣን ፡ ጋራ ፡ እንደዚሁ ፡ የንግድ ፡ ውል ፡ እዋዋላለሁ ፡ ብሎ ፡ ከነወታደሩ ፡ ሲሄድ ፡ ላፎሌ ፡ እሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ እጫካ ፡ ውስጥ ፡ ሱማሌዎች ፡ አግኝተው ፡ ከነተከታዮቹ ፡ በደፈጣ ፡ ገደሉት ፤ በጥርጣሬ ፡ ያስገደለውም ፡ ያው ፡ የጋለዲ ፡ ሡልጣን ፡ ነው ፡ ይባላል ።

እንደዚሁ ፡ በስለላ ፡ የተደበቀ ፡ አገርና ፡ ወንዝ ፡ አግኝተው ፡ ባገራቸው ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ለመመስገን ፡ የሚፈልጉ ፡ የኢጣሊያ ፡ ጕበኞች ፡ እየመጡ ፡ ብዙዎቹ ፡ በበረሓ ፡ ሙተዋል ። ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ ኤውጄኔዎ ፡ ሩስ



ፓሌ ፡ የሚባለው ፡ የጁባን ፡ ወንዝ ፡ እመረምራለሁ ፡ ሲል ፡ ባ፲፰፻፹፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እስከ ፡ ቦረና ፡ ጫፍ ፡ ድረስ ፡ ዘልቆ ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ በኬንያና ፡ በኢትዮጵያ ፡ አዋሳኝ ፡ አገር ፡ ካለው ፡ ጫካ ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ደርሶ ፤ ዝኆን ፡ አግኝቶ ፡ ለማደን ፡ ሲፈትን ፡ ወዲያው ፡ ዝኆኑ ፡ መቀመጫውን ፡ ጫካ ፡ የሚሰልልበትን ፡ ጣሊያን ፡ ሰባብሮ ፡ ገደለው ። እንዲሁም ፡ የሱ ፡ ጓደኛ ፡ ካፒቴን ፡ ቢቶሪዮ ፡ ቦቴጎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ የሚገኘውን ፡ የኦሞን ፡ ወንዝ ፡ መነሻውንና ፡ መድረሻውን ፡ ለመመርመር ፡ ሌሎችንም ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶች ፡ አስከትሎ ፡ ሩስፓሌ ፡ የሄደበትን ፡ ዱካ ፡ እየተከተለ ፡ ሄዶ ፡ ሩስፓሌ ፡ የሞተበትንና ፡ ዐፅሙ ፡ የተቀበረበትን ፡ ስፍራ ፡ ጐብኝቶ ፡ አለፈ ። ከዚያም ፡ በጎፋ ፡ አልፎ ፡ ወለጋ ፡ እደጃዝማች ፡ ጆቴ ፡ አገር ፡ በተለይ ፡ ጐቢ ፡ እሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ደርሶ ፡ ሌሊት ፡ እሰፈረበት ፡ ላይ ፡ ጋሎች ፡ አግኝተውት ፡ ባ፲፰፻፹፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመጋቢት ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ጦርነት ፡ አደረጉ ፤ በዚህም ፡ ውጊያ ፡ ከውስጣቸው ፡ ፪ ፡ ቴኔንቴዎች ፡ ተማርከው ፡ እጃቸውን ፡ ሲሰጡ ፡ ካፒቴን ፡ ቦቴጎና ፡ የቀሩት ፡ ሁሉም ፡ እዚያው ፡ እጦርነት ፡ ላይ ፡ ሞቱ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከመቃዲሾ ፡ ግዛቱን ፡ ለማስፋት ፡ እስከ ፡ ባርደሌ ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ ሉክ ፡ ከነበሩት ፡ ከደጃች ፡ አሰፋ ፡ ሉል ሰገድ ፡ ጋራ ፡ ተገናኘ ። ወዲያው ፡ ቡር ፡ አቃባ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባንዲራ ፡ ተተክሎ ፡ ነበርና ፡ ካፒቴን ፡ ቦንጂዎባኒ ፡ የሚባለው ፡ ብዙ ፡ የኤርትራን ፡ ወታደሮች ፡ ጭምር ፡ አስከትሎ ፡ ግዛቱ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ነውና ፡ የባርደሌን ፡ ስፍራ ፡ ልቀቁልኝ ፡ ሲል ፡ ከደጃች ፡ አሰፋ ፡ ሉል ፡ ሰገድ ፡ ጋራ ፡ ባ፲፱፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ውጊያ ፡ ዠመረ ፤ ደጃች ፡ አሰፋም ፡ አለቅም ፡ በማለት ፡ ተዋግተው ፡ የነበረበትን ፡ ምሽግ ፡ ጭምር ፡ አስለቅቀው ፡ አባረሩት ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ የሱማሊያን ፡ አገር ፡ ከኢጣሊያም ፡ ከእንግሊዝም ፡ ከኢትዮጵያውያንም ፡ እየተዋጋ ፡ ይከላከል ፡ የነበረው ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ የኖጋሉ ፡ ባላባት ፡ ሙላህ ፡ እሚባለው ፡ ከእንግሊዝ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተዋጋ ፡ ፩ ፡ ጊዜም ፡ ድል ፡ ሲያደርግ ፡ ፩ ፡ ጊዜም ፡ ድል ፡ ሲሆን ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ባ፲፱፻፲፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአየር ፡ ጦርነት ፡ ጭምር ፡ ወግተውት ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ለኢጣሊያ ፡ የተመቸ ፡ ጊዜ ፡ ሆነለት ፤ ወዲያው ፡ ብዙ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አዘጋጅቶ ፡ በጠባቂነት ፡ ስም ፡ ይዞት ፡ ቈይቶ ፡ የነበረውን ፡ የኦቢያንና ፡ የማጁርቲንን ፡ አገር ፡ ውሉን ፡ አፍርሶ ፡ ቀጥቅጦ ፡ ለመግዛትና ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ለማድረግ ፡ በነዚሁ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ ተዠመረ ። እነ

ሱም ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ አንሆንም ፡ በማለት ፡ ፊት ፡ ለፊትም ፡ እየተደበቁም ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ በመሣሪያና ፡ በወታደር ፡ ብዛት ፡ ድል ፡ ስላ ደረጋቸው ፡ ገሚሶቹ ፡ ተስፋ ፡ በመቊረጥ ፡ ተገዥነታቸውን ፡ እያመኑ ፡ ገቡ ለት ፤ የቀሩት ፡ ግን ፡ አገራቸውን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ እየ ተሰደዱ ፡ ተቀመጡ ።

ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ሱማሊያን ፡ እስከ ፡ ለቀቀበት ፡ ድረስ ፡ በታሪኩም፡ በመሬቱም ፡ አቀማመጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሱማሌ ፡ ሊባል ፡ የሚገባው ፡ አገር ፡ የኢጣሊያ ፡ ሱማሌ ፡ እየተባለ ፡ ዓርባ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ወንዶቹም ፡ ሴቶ ቹም ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ ከጢት ፡ ዠምረው ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ከኢጣሊያ ፡ አገር ፡ እየመጡ ፡ በሱማሊያ ፡ የተቀመጡትን ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ለማክበር ፡ ሲሠ ሩና ፡ ሲለፉ ፡ መኖራቸውን ፡ ይኸን ፡ መጽሐፍ ፡ የጻፈው ፡ ባ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በግዞት ፡ መዠመሪያ ፡ ደናኔ ፡ ከዚያም ፡ ፲፲፮ ፡ የሙዝ ፡ እርሻ ፡ (ኮንሴሲ ዮን) ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ወደ ፡ ገናሌ ፡ ሄዶ ፡ ባይኑ ፡ አይቷል ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፯ ።

### የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ኀይል ፡ መሰብሰብና ፡ ግዛት ፡ ማስፋት ።

ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ከያለበት ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እየሰበሰቡ ፡ ወታደራቸውን ፡ ያደ ራጁ ፡ ነበር ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥትም ፡ ተላልከው ፡ አሥር ፡ ሺህ ፡ ጠመንዣ ብዙ ፡ ጥይት ፡ ካገኙ ፡ ወዲህ ፡ እንዲሁም ፡ የዐድዋ ፡ ዘመቻ ፡ ሊደረግ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ሲቀረው ፡ በነሙሴ ፡ ሽፍኒ ፡ አማካይነት ፡ ከፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ብዙ ፡ መሣሪያ ፡ በግዥ ፡ አግኝተዋል ።

ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በዚሁ ፡ ከኢጣሊያኖች ፡ ባገኙት ፡ መሣሪያ ፡ ኢጣሊ ያኖችን ፡ አባረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ እስከ ፡ መረብ ፡ ድረስ ፡ መሆኑን ፡ ከጦርነቱ ፡ ወዲህ ፡ በስምምነት ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከተዋዋሉ ፡ በኋላ ፡ ከዚያም ፡ በፊት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ደቡብ ፡ ያለውን ፡ ታላቁን ፡ የሐረርን ፡ ግዛት ፡ ራሳቸው ፡ ሄደው ፡ ባ፲፰፻፸፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ አሚር ፡ ዐብዱላሂን ፡ ወግ ተው ፡ አስመልሰው ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ አሚር ፡ ዐብዱላሂ ፡ ተሸንፎ ፡ እጁን ፡ ስለ ፡ ሰጠ ፡ አገሩን ፡ በቅንና ፡ በትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ እንዲያስተዳድሩ ፡ ራስ ፡ መኰንንን ፡ ደጃዝማች ፡ ብለው ፡ ሾመው ፡ ሐረር ፡ ትተዋቸው ፡ ተመልሰው ፡



እቴጌ ፡ ጣይቱ ።

እንደ ፡ ነበረ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ተናግረናል ። ርሳቸውም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ ከሐረር ፡ ወዲያ ፡ ኢሳንና ፡ ውጋዴን ፡ አልፎ ፡ እስከ ፡ ሱማሊያ ፡ ወሰን ፡ ድረስ፡ አቀኑ ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ተዠምሮ ፡ የቈየውን ፡ አገር ፡ ለመያዝ ፡ እንዲሁ ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ቍጥሩ ፡ ፴ ፡ ሺህ ፡ የሚደርስ ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ አስከ ትለው ፡ ከፋሌ ፡ ዠምረው ፡ የሺሆጄሌን ፡ ግዛት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አድር ገው ፡ እስከ ፡ ሱዳን ፡ ጠረፍ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ አስገበሩ ።

ደጃች ፡ ተሰማ ፡ ናደው ፡ በይሉባቦር ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ የባሮን ፡ መሬት ፡ እያቋረጡ ፡ እስከ ፡ ሶባትና ፡ እስከ ፡ ነጭ ፡ አባይ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ አስገበሩ ።

ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከፋን ፡ ኵሎን ፡ ኰንታን ፡ ሊሙን ፡ ከዚያም ፡ እስከ ፡ ነጭ ፡ ዓባይ ፡ ድረስ ፡ አልፈው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ አሰፉ ።

ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ፲፰ ፡ ሺሕ ፡ ያኽል ፡ የጦር ፡ ወታደራቸ ውን ፡ ይዘው ፡ በቦረና ፡ በኩል ፡ እስከ ፡ ኬንያ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ አቀኑ።

እነዚህ ፡ እላይ ፡ የተቈጠሩት ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ጊዜ ፡ ለጌታቸው ፡ በቅን ነት ፡ እያገለገሉ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ በማስፋታቸው ፡ ታላቅ ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፰ ።

ስለ ፡ ወይዘሮ ፡ ባፈና ፡— ስለ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡— ስለ ፡ ራስ ፡ ዳርጌ ፡— ስለ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡— ስለ ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡— ስለ ፡ ራስ ፡ በዛብኽ ፡— ስለ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡— ስለ ፡ ራስ ፡ ወሌ ።

### ስለ ፡ ወይዘሮ ፡ ባፈና ።


ወይዘሮ ፡ ባፈና ፡ ትውልዳቸው ፡ መርሐ ፡ ቤቴ ፡ ከባላባት ፡ ወገን ፡ ነው ። ከዐፄ ምኒልክ ፡ ከተጋቡ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ሴቶች ፡ ለባላቸው ፡ ክብር ፡ በመቅ ናትና ፡ ባላቸውን ፡ በማገልገል ፡ ፈንታ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ባላን ጦች ፡ ከነደጃች ፡ መሸሻ ፡ ሰይፉ ፡ ካማቻቸው ፡ ከይማም ፡ መሐመድ ፡ ጋራ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ እየተላላኩ ፡ በባለቤታቸው ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ላይ ፡ ዐድማ ይሠሩባቸው ፡ ነበር ። እንደዚሁም ፡ በዐፄ ፡ ዮሐንስና ፡ በንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ መካከል ፡ ግጭት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አሳባቸውን ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ እያደረጉ ይስማሙ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ይኸንንም ፡ ቢያ ውቁ ፡ ፍቅር ፡ የማያሸንፈው ፡ ነገር ፡ አይገኝምና ፡ ክዳታቸውንና ፡ ዐድማቸ ውን ፡ በፍቅር ፡ ምክንያት ፡ እየታገሡ ፡ አብረው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ወይዘሮ ፡ ባፈና ፡ ይኸንኑ ፡ ያድማ ፡ ነገር ፡ እየቀጠሉ ፡ ስለ ፡ ሄዱ ፡ ባ፲፰፻፸፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጭራሽ ፡ ፈቷቸው ።



### ስለ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ።

የየጁ ፡ ባላባት ፡ የደጃች ፡ ብጡል ፡ ልጆች ፡ ልጅ ፡ ወሌና ፡ ልጅ ፡ አሉላ ፡ የሚ ባሉት ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በኋላ ፡ ለዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ አሽ ከርነት ፡ ስላደሩ ፡ ልጅ ፡ ወሌ ፡ የደጃዝማችነት ፡ ልጅ ፡ አሉላ ፡ የፊታውራሪ ነት ፡ ማዕርግ ፡ አግኝተው ፡ ከየጁ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መጥተው ፡ በከበሬታ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ወይዘሮ ፡ ጣይቱ ፡ እኅታቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ደስታን ፡ አስከት ለው ፡ ወንድሞቼን ፡ አያለሁ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መጥተው ፡ በደጃች ፡ ወሌ ፡ ቤት ፡ ተቀመጡ ። ዐፄ ፡ ምኒልክም ፡ በጐንደርና ፡ በመቅደላ ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ የወይዘሮ ፡ ጣይቱን ፡ ውበትና ፡ ጠባይ ፡ ይሰሙ ፡ ነበርና ፡ በሸዋ ፡ መጥ ተው ፡ በደጃች ፡ ወሌ ፡ ቤት ፡ በመቀመጣቸው ፡ ደስ ፡ ስላላቸው ፡ አዲስ ፡ በመ ጡት ፡ በአቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ እጅ ፡ በሺህ ፡ ፰፻፸፭ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ሚያ ዝያ ፡ ፳፭ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ሥጋ ፡ ወደሙ ፡ ተቀብለው ፡ ተጋቡ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፮ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ አብረው ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ባ፲፰፻፹፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘውድ ፡ በደፉ ፡ ጊዜ ፡ ወይ ዘሮ ፡ ጣይቱም ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ በጳጳሱ ፡ በአቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ እጅ ፡ የሚገ ባቸውን ፡ ዘውድ ፡ ደፍተው ፡ እቴጌ ፡ ተባሉ ፡ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ እየተባሉ ፡ ይጠሩ ፡ ዠመር ።

እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ባላቸውንና ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚወዱ ፡ ናቸው ፡ በመልካ ቸውም ፡ በጣም ፡ የተዋቡና ፡ ባለሙያ ፡ ጠባየ ፡ መልካም ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ይወዷቸውና ፡ ያከብሯቸው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ እቴጌ፡ የጠሉት ፡ ይነቀፋል ፡ ከሹመትም ፡ ይሻራል ፡ የወደዱትም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ፡ ዘንድ ፡ ክብርና ፡ ሞገስ ፡ ሹመትም ፡ ያገኛል ። ስለዚህ ፡ መሳፍንቱና ፡ መኳን ንቱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ እንደሚፈሩና ፡ ደጅ ፡ እንደሚጠኑ ፡ እንዲሁ ፡ እቴጌ ዪቱንም ፡ ደጅ ፡ ይጠኑ ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ የውጫሌ ፡ ውል ፡ ያ፲፱ኛው ፡ አን



ራስ ፡ መንገሻ ፡ ዮሐንስ ።



ቀጽ ፡ ንግግር ፡ እንዲለወጥ ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክና ፡ በኮንቴ ፡ አንቶኔሊ ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ ሲደረግ ፡ እቴጌዪቱም ፡ በክርክሩ ፡ እየገቡ ፡ ይነጋገሩበት ፡ ነበር ።

በኋላም ፡ ባ፲፯ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ንግግር ፡ ፈንታ ፡ «የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከመሬቱ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ባ፲፯ኛው ፡ አንቀጽ ፡ የተባለውን፡ ጥገኝነት ፡ ለሌላ ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ እንዳይሰጥ ፡ ግዴታ ፡ ይግባና ፡ ይለወጥ» ፡ ብሎ ፡ ሲያቀርብ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይኸንኑ ፡ አሳብ ፡ ከራስ ፡ መኰንን ፡ ጋራ ፡ ሲመካከሩ ፡ እቴጌዪቱ ፡ የፈቀድነውን ፡ ብናደርግ ፡ የኛ ፡ የግል ፡ ሥልጣናችን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እሱን ፡ በፍጹም ፡ የሚያገባው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ብለው ፡ ውሉ ፡ እንዲቀር ፡ አደረጉ ።

በኋላም ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ የዐድዋ ፡ ዘመቻ ፡ በተቀሰቀሰ ፡ ጊዜ ፡ የግል፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ ዘምተው ፡ ተዋጊውን ፡ ወታደር ፡ ሲያበረቱ ፡ ውለዋል ።

የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎችም ፡ የዐድዋንና ፡ የዐፄ ፡ ምኒልክን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ታሪክ ፡ ሲጽፉ ፡ የእቴጌ ፡ ጣይቱን ፡ ስም ፡ እያገነኑ ፡ ጽፈውላቸዋል ።

## ስለ ፡ ራስ ፡ ዳርጌ ።

ራስ ፡ ዳርጌ ፡ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልጅ ፡ ናቸው ። ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሸዋን ፡ ለማስገበር ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክን ፡ ይዘው ፡ ሲመለሱ ፡ ራስ ፡ ዳርጌ ፡ በሸዋ ፡ ቀርተው ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ አቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ መታሠር ፡ ላቢቴታ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ሄደው ፡ ነበርና ፡ በዚያው ፡ ሳሉ ፡ አቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ ከታስሩበት ፡ ቢያመልጡ ፡ ተጠርጥረው ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜያት ፡ ታሠሩ ፡ በኋላም ፡ እሥራቱ ፡ ቀርቶላቸው ፡ በደጅ ፡ ጥናት ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ለሸዋ ፡ እንደራሴ ፡ ሊያደርጓቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይሸፍትብዎታል ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ መከሯቸው ፡ በጥርጣሬ ፡ አስቀሩባቸው ። በዚያም ፡ ሲኖሩ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ መኳንንቱን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስበው ፡ በመቅደላ ፡ ሲያሥሩ ፡ እንደዚሁ ፡ ራስ ፡ ዳርጌንም ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ አሠሯቸው ። ከዚያም ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ አምልጠው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ዳርጌ ፡ በዚያው ፡ በእሥር ፡ ቤት ፡ ቈዩ ።

ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ እንግሊዞች ፡ እሥረኛውን ፡ ሁሉ ፡ በያገሩ ፡ እንዲገባ ፡ ለቀውት ፡ ነበርና ፡ ራስ ፡ ዳርጌም ፡ ወዳገራቸው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ተመልሰው ፡ በመከበርና ፡ በመፈራት ፡

ሲገዙ ፡ ኖሩ ። የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልጅ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ እንደነ ፡ ደጃች ፡ መሸሻ ፡ ሰይፉ ፡ እንደነ ፡ ፊታውራሪ ፡ ጉልላቴ ፡ ዙፋንን ፡ ሳይ ቀናቀኑ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ በመተማመንና ፡ በመ ፋቀር ፡ ኖሩ ። ስለዚህ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ አክብረው ፡ በአባትነት ፡ ዐይን ፡ ይመለ ከቷቸው ፡ ነበር ።

## ስለ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ዮሐንስ ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ መተማ ፡ በጦርነቱ ፡ ውስጥ ፡ ቈስለው ፡ ሳሉ ፡ ከዕረፍታቸው ፡ በፊት ፡ አልጋዬን ፡ የሚወርሰው ፡ ልጄ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ነውና ፡ ለርሱ ፡ ተገዙ፡ ብለው ፡ ለመኳንንቶቻቸው ፡ አስታውቀው ፡ ነበር ፡ ስለዚህ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒ ልክ ፡ በመላዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ይሸፍታሉ ፡ እየተባለ ፡ ሲወራ ፡ ሳይሸፍቱ ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ተገናኙ ፡ ንጉ ሡም ፡ በዚሁ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ የትግሬን ፡ ግዛት ፡ መልሰው ፡ ሰጧቸው ፡ በዐ ድዋም ፡ ዘመቻ ፡ ጊዜ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጐን ፡ ተሰልፈው ፡ ኢጣሊያኖችን ፡ በመውጋት ፡ ታላቅ ፡ ሞያ ፡ ሠርተዋል ፡ ሚስታቸውም ፡ የእቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ወን ድም ፡ የራስ ፡ ወሌ ፡ ልጅ ፡ ወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ነበሩ ።

በኋላ ፡ ግን ፡ ባንዳንድ ፡ መካሮቻቸው ፡ ተመርተው ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ላይ ፡ ሸፈቱ ፡ ሲሸፍቱም ፡ ውስጡን ፡ ከራስ ፡ ስብሐትና ፡ ከደጃዝማች ፡ ሐጐስ፡ ተፈሪ ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ለመሆን ፡ ተስማምተው ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ራስ ፡ መኰንንን ፡ ባ፲፰፻፸፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላኳቸው ። እርሳቸውም ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ በቆቦና ፡ በአሸንጌ ፡ በኩል ፡ አልፈው ፡ አላጌ ፡ ደረሱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ከተማመኑባ ቸው ፡ አንዱ ፡ ደጃች ፡ ሐጐስ ፡ በአጋሜ ፡ ግዛት ፡ ከራስ ፡ ስብሐት ፡ አይዋደ ዱም ፡ ነበርና ፡ ራስ ፡ መንገሻን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ መጥተው ፡ የአ ጋሜን ፡ ግዛት ፡ አገኙ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ያላቸው ፡ ኀይል ፡ የራስ ፡ መኰንንን ፡ ጦር ፡ ለመመለስ ፡ አለመቻሉን ፡ ተረድተውት ፡ እጃቸ ውን ፡ ለራስ ፡ መኰንን ፡ ሰጡ ።

ራስ ፡ መኰንንም ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ምሕረት ፡ እንዲያደርጉላቸው ፡ የል መና ፡ ደብዳቤ ፡ ጨምረው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ላኳቸው ። ራስ ፡ መንገሻም ፡ ከት ግሬ ፡ ተነሥተው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥተው ፡ እንዲምሯቸው ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡



ምኒልክ ፡ ገቡ ። ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ሸፍተኽ ፡ ሳይሳካልኽ ፡ ቢቀር ፡ ወደኔ ፡ መጣኽ ፡ አሁንም ፡ ምሕረት ፡ ባደርግልኽ ፡ ፫ኛ ፡ ሸፍተኽ ፡ የረጋውን ፡ መንግሥቴን ፡ ታነቃንቃለኽ ፡ ብለው ፡ በግዞት ፡ ወደ ፡ አንኮበር ፡ ላኳቸው ።

የትግሬንም ፡ ግዛት ፡ እንዲያስተዳድሩ ፡ ለራስ ፡ መኰንን ፡ ሰጧቸው ፡ ራስ ፡ መኰንንም ፡ ፩ ፡ ዓመት ፡ ከ፯ ፡ ወር ፡ ያኽል ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ አገሩን ፡ ለራስ ፡ ወሌ ፡ አስረክበው ፡ ባ፲፰፻፺፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ።

## ስለ ፡ ራስ ፡ መኰንን ።

ራስ ፡ መኰንን ፡ የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ አክሥት ፡ የወይዘሮ ፡ ተናኘ ፡ ወርቅ ፡ ልጅ ፡ ናቸው ። አባታቸውም ፡ የወግዳና ፡ የዶባ ፡ ባላባት ፡ ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ሚካ ኤል ፡ ናቸው ።

ከሕፃንነታቸው ፡ ዠምሮ ፡ በትምህርት ፡ ያደጉ ፡ ከመሆናቸው ፡ በስተ ቀር ፡ በተፈጥሮ ፡ ካገኙት ፡ ጠባያቸው ፡ አስተዋይና ፡ ታጋሽ ፡ ነበሩ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የጌታ ፡ ወንድማቸው ፡ ለሆኑት ፡ ለዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ በፍቅርና ፡ በእ ምነት ፡ ስለሚያገለግሉ ፡ በጣም ፡ ይወዷቸው ፡ ነበርና ፡ ሌሎችና ፡ ይልቁንም ፡ የሚያፈቅሯቸው ፡ ባለቤታቸው ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ የራስ ፡ መኰንንን ፡ አገልግ ሎት ፡ ለማሳነስና ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ ለማጣላት ፡ ቢጥሩ ፡ በፍጹም ፡ አል ሆነላቸውም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ከባድ ፡ የሆነውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ያስተዳዳሪ ነት ፡ ቀንበር ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ በተሸከሙበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ከሌሎቹ ፡ መኳን ንቶች ፡ ይበልጥ ፡ ያግዟቸው ፡ የነበሩት ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ማስተዳደሩ ፡ ችግር ፡ መስሎ ፡ ይታይ ፡ የነበረውን ፡ የሐረርጌንና ፡ የት ግሬን ፡ ግዛት ፡ በማስተዳደር ፡ ይመሰገኑ ፡ ነበር ።

በምዕራብም ፡ ኢትዮጵያ ፡ እስከ ፡ አቢጋር ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ አቅ ንተዋል ። በዐድዋም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የአምባ ፡ አላጌንና ፡ የመቀሌን ፡ ምሽግ ፡ አስለቅቀው ፡ የዐድዋ ፡ ዕለትም ፡ ዠግንነታቸው ፡ ታውቋል ። እንዲሁም ፡ ወደ ፡ እንግሊዝና ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እየተላኩ ፡ ሄደው ፡ ብዙ ፡ ጉዳይ ፡ ፈጽመዋል ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የአክሥታቸው ፡ ልጅ ፡ ከመሆን ፡ በስተቀር ፡ በወታደርነት ፡ ባገር ፡ አስተዳዳሪነት ፡ በዲፕሎማቲክ ፡ ጭምር ፡

በሚያደርጉላቸው ፡ አገልግሎት ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ከልብ ፡ ስለ ፡ ወደዷቸውና ፡ ስላመኗቸው ፡ ከኔ ፡ በኋላ ፡ አልጋዬን ፡ አወርሳለሁ ፡ እያሉ ፡ ያስቡ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አሳባችሁ ፡ ካሳቤ ፡ መሬት ፡ ከሰማይ ፡ የሚርቀውን ፡ ያኽል ፡ ይራራቃል ፡ ብሎ ፡ ለነቢዩ ፡ ለኢሳይያስ ፡ የተናገረው ፡ አምላክ ፡ የወራሹን ፡ ሕይወት ፡ ከአውራሹ ፡ በማስቀደሙ ፡ የቀረ ፡ አስመስሎ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ለልጃቸው ፡ አልፎ ፡ እንዲጠበቅ ፡ የመለኮትነቱ ፡ ፈቃድ ፡ ሆነ ። ራስ ፡ መኰንንም ፡ የሞቱት ፡ ባ፲፰፻፺፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ መጋቢት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ነው ።

ስለ ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተገጠመ ።

የራስ ፡ መኰንን ፡ ልብሱ ፡ ሁሉ ፤
እጀ ፡ ሰፊ ፡ ነው ፡ አሉ ፡ (ቦልቦሌ ፤)
እጀ ፡ ጠባብን ፡ እየናቀ ፤
ሳያጠልቀው ፡ ዘለቀ ።
መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ ተጠባብቆ ፤
ወርቁን ፡ አልናኘም ፡ ደብቆ ፤
በተናኘ ፡ ወርቅ ፡ ሐረርጌን ፤
ገዛ ፡ አሉ ፡ መኰንን ።
ራስ ፡ መኰንን ፡ መሐንዲሱ ፤
ይለዋል ፡ ሁሉም ፡ በየራሱ ፤
አስደለደለው ፡ መንገዱን ፤
መንጥሮ ፡ ውጋዴን ።
ሊቀ ፡ መልአኩ ፡ መቅደስ ፡ ገብቶ ፤
ድጓውን ፡ አዘርግቶ ፤
መኰንን ፡ ቃኘው ፡ አለው ፤
ሁሉ ፡ እንዲቀበለው ።
ራስ ፡ መኰንን ፡ ሲሔድ ፤
ትልቅ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ በመንገድ ፤
የምኒልክ ፡ ቀኝ ፡ አሉት ፤
ሲወረውር ፡ ቢያዩት ።
የወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ልጅ ፡ ያረቄ ፡ መርፌው ፡
ያበሻን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ጠቃቅሞ ፡ ጠቃቅሞ ፡
እንጀራ ፡ አበላው ።



በሞቱ ፡ ጊዜ ።
ሲታሰር ፡ አየነው ፡ ብረቱ ፡ ሲመታ ፤
ምን ፡ ዋስ ፡ አገኘና ፡ ሐረርጌ ፡ ተፈታ ።
ጃንሆይ ፡ ምኒልክ ፡ ጠጕራቸው ፡ ሣሣና ፡ በራ ፡ ገለጣቸው ፡
እንግዴህ ፡ ንጉሡ ፡ ምን ፡ ራስ ፡ አላቸው ።

ስለ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ።

ራስ ፡ ሚካኤል ፡ የወሎ ፡ ባላባት ፡ ናቸው ። ባገልግሎታቸው ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስን ፡ ደስ ፡ አሰኝተው ፡ ነበርና ፡ ባ፲፰፻፸ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መሐመድ ፡ የሚባለውን ፡ ስማቸውን ፡ አስለውጠው ፡ ሚካኤል ፡ አሰኝተው ፡ የክርስትና ፡ ልጅ ፡ አድርገው ፡ በክብር ፡ ያኖሯቸው ፡ ነበር ። በኋላም ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ዐርፈው ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ አካሄዳቸውን ፡ ሳይለውጡ ፡ በዐድዋም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ሞያ ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ ልጃቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ሸዋ ፡ ረጋን ፡ ባ፲፰፻፺፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ድረው ፡ ባለሚል ፡ አደረጓቸው ።

ስለ ፡ ራስ ፡ በዛብኽ ።

ራስ ፡ በዛብኽ ፡ የንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ ናቸው ። ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከእምባቦ ፡ ዘመቻ ፡ ወዲህ ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ በፍቅር ፡ ሲኖሩ ፡ ባ፲፰፻፺፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ጥር ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ዐርፈው ፡ በከተማቸው ፡ በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ተቀበሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በሕይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ ይገዙት ፡ የነበረውን ፡ ሰፊ ፡ ግዛት ፡ ለመግዛት ፡ ካባታቸው ፡ ተቀያይመው ፡ በሸዋ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩት ፡ የበኵር ፡ ልጃቸው ፡ ራስ በዛብኽ ፡ የማይመጥኑ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ዳሞትን ፡ አገው ፡ ምድርን ፡ ሜጫን ፡ አቸፈርን ፡ አንሥተው ፡ ለራስ ፡ ቢትወደድ ፡ መንገሻ ፡ አቲከም ፡ ሰጥተው ፡ የጐጃምን ፡ ግዛት ፡ ለራስ ፡ በዛብኽ ፡ ሰጧቸው ። ወዲያውም ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ የልጃቸውን ፡ የወይዘሮ ፡ ሸዋ ፡ ረጋን ፡ ልጅ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበ ፡ ወርቅን ፡ በሚስትነት ፡ ዳሩላቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ጋራ ፡ መጋባታቸው ፡ ደስ ፡ ቢያሰኛቸው ፡ ያባታቸው ፡ ግዛት ፡ የነበረው በመከፈሉ ፡ ቅር ፡ ብሏቸው ፡ ነበርና ፡ በዚሁ ፡ ስለ ፡ ሸፈቱ ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ አፍቀራ ፡ ተላኩ ።

## ስለ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ።

ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልጅ ፡ የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ አክሥት ፡ የወይዘሮ ፡ አያኽሉሽም ፡ ልጅ ፡ ናቸው ። አባታቸውም ፡ አቶ ፡ አቦዬ ፡ ይባላሉ ። ዕድገታቸው ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ቤት ፡ ስለሆነ ፡ በታማኝነትና ፡ በመታዘዝ ፡ ለጌታቸው ፡ አገልግለዋል ። ይኸውም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተባለውን ፡ ከፋን ፡ ሡሎን ፡ ኲንታን ፡ ሊሙን ፡ ስላቀኑ ፡ በከፋ ፡ የራስነት ፡ ማዕርግ ፡ አግኝተዋል ። ከዚያም ፡ እስከ ፡ ነጭ ፡ አባይ ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ ተክለዋል ።

ንጉሥ ፡ ከተባሉ ፡ ወዲህ ፡ የተገጠመላቸው ።

የንጉሥ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡

አባ ፡ ሰጉድ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፤
የሡሎው ፡ ደጃዝማች ፡ የከፋው ፡ ራስ ፡
ዘውዲቱን ፡ ተመኝ ፡ ዝምድና ፡ ሊያፈርስ ።
ሰጉድ ፡ ሃይማኖቱን ፡ እያስመሰከረ ፤
ጠመንጃ ፡ አልተኰሰ ፡ ጦር ፡ አልወረወረ ፤
ሡሎንና ፡ ከፋን ፡ በዘንግ ፡ አስገበረ ።
ግብር ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ የላዩም ፡ የታቹ ፤
በዘንግ ፡ ተሰብስበው ፡ መጥተው ፡ ቢከማቹ ፤
ካህን ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ያሙታል ፡ ሰዎቹ ።

ፊት ፡ ሡሎንና ፡ ኲንታን ፡ አቅንተው ፡ ከፋን ፡ ሰጥተው ፡ አስለቅቀዋቸው ፡ ነበር ። ኋላ ፡ ደግሞ ፡ ራስ ፡ ተሰማ ፡ በልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ሞግዚትነት ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ስለሆኑ ፡ በክረምት ፡ ከፋን ፡ አስለቅቀው ፡ ጐንደር ፡ ቢሰዷቸው ፡ ገጣሚ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

አባ ፡ ሰጉድ ፡ ወልዴ ፡ ሆድህን ፡ ሆድ ፡ አይባሰው ፤
ወትሮም ፡ ልማድህ ፡ ነው ፡ እያቀናህ ፡ ለሰው ፤





መተማና ፡ ከሰላ ፡ ይመጣሉ ፡ ብሎ ፡ አዳምጦ ፡ ነበረና ፡

ሁሉን ፡ እየገዛህ ፡ ብትገሠግሥ ፤
ጐንደር ፡ ዘውድ ፡ ገዝተህ ፡ ከሆንክ ፡ ንጉሥ ፤
አንድ ፡ ዓረብ ፡ ቀርቶሃል ፡ የጐራዴህ ፡ ልብስ ።
ያባ ፡ ሰጉድ ፡ ጠዶ ፡ የጣና ፡ ባሕር ፤
ቢቀዱት ፡ ቢቀዱት ፡ አይጐል ፡ ዘወትር ፤
ከፋ ፡ ተበጥብጦ ፡ ተጠጣ ፡ ጐንደር ።

ዓፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከደብረ ፡ ታቦር ፡ ጀምሮ ፡ የቈረቈሩት ፡ ከተማ ፡ ፳ ፡ ነበር ። ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ ደንቀዝን ፡ መርጠው ፡ ቦታነቷ ፡ ፩ ፡ ማዕዘን ፡ የምታሳይ ፡ ስለሆነች ፡ ዋና ፡ ከተማቸውን ፡ እሷን ፡ አድርገው ፡ ነበር ። ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስም ፡ ከጠፋች ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ስላደሷት ፡ ገጣሚ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ተመርጣ ፡ የነበር ፡ ከሐያ ፡ ከተማ ፤
ደንቀዝ ፡ ጠፋችና ፡ ድምጧ ፡ ሳይሰማ ፤
እንደገና ፡ አበበች ፡ በሰጉድ ፡ ዓላማ ።
እንደ ፡ ድብ ፡ አንበሳ ፡ ተፈራ ፡ ግርማህ ፤
ደንቀዝ ፡ ቢያጉረመርም ፡ ሰጉድ ፡ ፈረስህ ፤
ተሸበረ ፡ አሥመራ ፡ መስሎት ፡ የመጣህ ።

ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቈራጭ ፡ ይሁኑ ፡ በተባለ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ አዝማሪ ።

እጅግ ፡ ያምር ፡ ነበር ፡ የራስ ፡ ቈንደላቸው ፤
ቶሎ ፡ እንዲሽብቱ ፡ ለምን ፡ ቈረጧቸው ።

## ስለ ፡ ራስ ፡ ወሌ ።

ራስ ፡ ወሌ ፡ ብጡል ፡ የእቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ታናሽ ፡ ወንድም ፡ የየጁ ፡ ባላባት ፡ ናቸው ። በዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ በጣም ፡ የተከበሩ ፡ ከመሆናቸው ፡ በስተቀር ፡ በዤግንነት ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተገጠመላቸው ።